# የአክራሪነት እንቅስቃሴን መድፈቅ የሚያስችል ጉባኤ

ክፍል ሁለት

አዲስ ቶልቻ 09/06/13

እንግዲህ በተመሳሳይ ርዕስ በቀረበው በክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ በተገለፀው አኳኋን ሁከት ለመቀስቀስ በአክራሪው ቡድን እንደምክንያት ለቀረቡት ጥያቄዎች በሙሉ ተገቢው መልስ የተሰጠ ቢሆንም፣ በፔትሮ ዶላር የናወዙት አክራሪዎች ወደሰላም ከመምጣት ይልቅ የሙስሊሙን ሰላማዊ የፀሎት ስርዓቶች በመበጥበጥ ፣ በደቡብ ወሎ ሃብሮ ወረዳና በአርሲ አሳሳና በኮፈሌ ከተሞች እንደሆነው፣ መሳሪያ ታጥቀው ዱላና ድንጋይ የያዙ ጀሌዎቻቸውን በማሰማራት መንግስታዊ ተቋማት ላይ፣ የህዝብ ሃብት ላይ እንዲሁም የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ላይ ጥቃት በመሰንዘር ሁከቱን ለማባባስ ሞክረዋል።

የትኛው ድምፃቸው እንደሚሰማ ለሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ግለፅ ባይሆንም በአገር ውስጥ፣ እንዲሁም የዋሃቢ ሰለፊ ቡድን አውራ ከሆነው የግብፁ ሙስሊም ብራዘር ሁድ ጋር በመሆን ባደራጁት "ድምፃችን ይሰማ" የተሰኘ ስብስብ በማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን በማሰራጨት ሁከትና ግርግሩን ለማቀጣጠል ቆርጠው ተነሱ።

ከዚሁ ጎን ለጎን ድሮ ሞቶ የተቀበረ በኢትዮጵያ አሃዳዊ መንግስት የመመስረትና፣ የምዕራባዊያንን አይዞሕ ባይነት እናገኛለን በሚል፣ ለአፍሪካ የማይበጅ መሆኑ በመረጋገጡ የተተፋው የኒዮሊበራሊዝም የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ላይ የተንጠለጠሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቀልባቸው አክራሪው ቡድን ላይ አርፏል፡፡ አብሮ ለመስራትም ፍጥምጥም ፈፅመዋል፡፡ ይህ መንግስትን በህገወጥ መንገድ ለማስወገድ ይጠቅመን ይሆናል በሚል ግምት ከአክራሪዎቹ ጋር አንዱ ሌላውን አለኝታ አድርገው የፈፀሙት ጋብቻ በሰላም ወዳድ ኢትዮጵያን ዘንድ የሚጎረብጥ ስሜት ፈጥሯል፡፡

ሰማያዊ የተሰኘው ፓርቲ፣ ገና የፓርቲው ስያሜ እንኳን መለኮታዊ ይሁን የቀለም መለያ ወይም ሌላ የተለየ ትርጉም ያለው መሆኑ በህዝቡ ዘንድ በወጉ ሳይታወቅ ተመስርቶ

ዓመት በወጉ እንኳን ሳይሞላው አክራሪውን ቡድን ራሱን ለማስተዋወቂያነት ተጠቅሞበታል። ፓርቲው በአዲስ አበባ የጠራው 5ሺህ ያህል በየሳምንቱ በአንዋር መስጊድ የሚካሄደውን የፀሎት ስነስርዓት የሚያውኩ የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪ ቡድን ጀሌዎች የተሳተፉበት የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄዱ ለዚህ ማሳያነት መጥቀስ ይቻላል።

የአክራሪውን ቡድን አጀንዳ በማንሳቱ አክራሪውን የዋሃቢ ሰለፊ ቡድን ከሙስሊም ብራዘር ሁድ ጋር በመሆን ባቀናበሩት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የወጡት የአክራሪ ጀሌዎች "አግንነውኛል" ብሎ ያሰበው ሰማያዊ ፓርቲ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት በመታየት ላይ የሚገኙት የአክራሪው ቡድን መሪዎች ካልተፈቱ ከሶስት ወር በኋላ ሌላ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚጠራም ዝቶ ነበር።

አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲም በከሰረ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ እንዲሁም በውስጡ ባለው ችግርና ከሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር መግባባት ባለመቻሉ የደረሰበትን ውድቀት የአክራሪው ቡድን ይጠግንልኛል የሚል ዕምነት የያዘ መሆኑን የሚያሳዩ እውነታዎች አሉ። አክራሪው ቡድን መልህቁን በጣለበት በደቡብ ወሎ ደሴ ከተማ የጠራው የተቃውሞ ሰልፍ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አንድ ሁለት ሺህ የሚሆኑ የአክራሪውን ቡድን ጀሌዎች አሰልፎ፣ ህገወጥ መፈክሮችን አሰምቶ አክራሪዎቹ በሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እንዲያላግጡ እድል ሰጣቸው።

ከዚህ በተጨማሪ በውጭ አገር ያለው "ድምፃችን ይሰማ" የተሰኘው የአክራሪዎች ቡደን ኢትዮጵያን የማተራመስ ተልዕኮና ይህን ተልዕኮ ማስፈፀሚያ ገንዘብ ከሻእቢያ ከተሰጠው ግንቦት 7 የተባለ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀ ቡድን ጋር፣ ውዥንብር መንዛታቸውን ተያይዘውታል።

እነዚህ ሁኔታዎች ቡድኑ እያደረ የሰላም ስጋት እየሆነ መምጣቱን ገሃድ አውጥተዋል። በመሆኑም ይህን ሃይማኖት ላይ ተለጥፎ እየተካሄደ ያለ የአክራሪነት እንቅስቃሴ ህዝቡ መንገድ እንዲዘጋበት ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው የመፍትሄ አማራጭ ሆኖ ተገኘ። በዚሁ መሰረት በመላው አገሪቱ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የአገር ሽማግሌዎች በየአካባቢያቸው የሰላም ኮንፈረንሰ አካሄዱ፡፡ በመጨረሻም ነሀሴ 21 እና 22

በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት አዳራሽ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት የሰላም የጋራ ጉባኤን አካሄዱ፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚወክሉ ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ የሃይማኖት መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች ታዋቂ ግለሰቦችና ምሁራን ተሳትፈዋል።

"የሃይማኖቶች አብሮነት እሴት በማጎልበት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በማክበር የአገራችንን የህዳሴ ጉዞ ለማሳካት እንረባረባለን" በሚል መሪ ሃሳብ በተካሄደው በዚህ ጉባኤ ላይ የአክራሪነትን አደጋዎች የሚያሳዩ፣ በኢትዮጰያ ከዚህ ቀደም ስለነበረውና አሁን ስላለው የሃይማኖትና የመንግስት ግንኙነት፣ ተቻችሎ ስለመኖር እሴቶች . . . ወዘተ የሚያስረዱ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል።

የጉባኤው ተሳታፊዎችም በአክራሪነት ምንነትና አደጋዎች ላይ በቂ ግንዛቤ አግኝተዋል፡፡ በጉባኤው ላይ የቀረቡትን ጥናታዊ ፅሁፎች ይዘት ሰፊ ስለሆነ እንዳስፈላጊነቱ በሌላ ፅሁፍ ለመመልከተ በይደር ትቼ ጉባኤው በመጨረሻ ካወጣቸው የአቋም መግለጫዎች ውስጥ በእኔ ግምት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ያልኩዋቸውን አራት ያህሉን ወደመመልከት ልሻገር።

ጉባኤው ካሳለፋቸው የአቋም  መግለጫዎች ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል በሚል የመረጥኳቸው፤ "ኢትዮጵያውያን የሚኮሩበትን በሃይማኖት ተቻችሎ፣ ተከባብሮ ፣ ተማምኖ አብሮ የመኖር አገራዊ እሴት በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ መንግስት፣ የሃይማኖት ተቋማትና፣ መላው ህዝብ ከፍተኛ ርብርብ እንዲያደርግ፤ የህግ የበላይነት አስተሳሰብ በላቀ ደረጃ እንዲገነባ የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ሕገመንግስትን የማወቅ፣ የማክበረና የማስከበር የዜግነት ድርሻችንን እንወጣለን፤ በሃይማኖት ሽፋን እያቆጠቆጠ የመጣውን የአክራሪነትና ጽንፈኝነት እንቅስቃሴ ምንም አይነት ሃይማኖታዊ መነሻ የሌለውና የጥቂት ቡድኖች ድብቅ ፖለቲካዊ ፍላጎት ለማሳካት ያለመ በመሆኑ ጉባኤው በጋራ ለማውገዝና ለመመከት የጋራ አቋም ይዟል፤ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለአገር ሰላም ጠንቅ ለሆነ የአክራሪ ኃይሎች የጥፋት መሳሪያ የሆኑ አንዳንድ ወገኖች አደጋውን በውል ተገንዝበው ከስህተታቸው ታርመው ለሰላምና ለልማት በፅናት እንዲቆሙ ጥሪ እናቀርባለን" የሚሉት ናቸው።

የእነዚህን የአቋም መግለጫዎች ይዘት አንድ በአንድ በአጭሩ እንመልከት። "ኢትዮጵያውያን የሚከብሩበትን በሃይማኖት ተቻችሎ፣ ተከባብሮ፣ ተማምኖ አብሮ የመኖር አገራዊ እሴት በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ለቀጣዩ ትወልድ እንዲተላለፍ መንግስት፣ የሃይማኖት ተቋማትና መላው ሕዝብ ከፍተኛ ርብርብ እንዲያደርጉ" ከሚለው ልጀምር።

መንግስት ሃይማኖቶችን ለያይቶ የእምነት መብትና ነፃነት በህገመንግስት በገደበበት የንጉሥ ነገስቱ ስርዓት፣ በህዝቡ መሃከል ከስርዓቱ ከሚከተለው ሕግ በተቃራኒ አንዱ የሌላውን ሃይማኖት አክብሮ፣ በጋራ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተማክሮ በመቻቻል አብሮ መኖሩን ኢትዮጵያን ሁሉ የሚመሰክሩለት እውነት ነው።

ይህ የሃይማኖቶች መከበርና መቻቻል ከቅርብ አመታት ወዲህ አደጋ የገጠመው መሆኑ ይፋ ከሆነ በኋላ በርካታ አረጋውያን በሰጡት ምስክርነት፣ ሙስሊሞች መስጊድ ሲሰሩ ክርስቲያኑ በጉልበት፣ በቁሳቁስና ፣ በገንዘብ ድጋፍ ያደርግ እንደነበረ፣ ቤተክርስቲያን ሲሰራም በሙስሊሞቹ በኩል ተመሳሳይ ትብብር ይደረግ እንደነበረ አስታውሰዋል። ክርስቲያኖች በድምቀት በሚያከብሩት የጥምቀት በኣል ላይ ታቦት ወጥቶ ሲገባ ሙስሊሞችም ከክርስቲያን ዘመዶቻቸውና ጎረቤቶቻቸው ጋር ታቦቱን ሸኝተው "አላሃምዲላላህ ታቦታችን በሰላም ገባ" ብለው የበአሉ ስርአት በሰላም ለመከናወኑ ፈጣሪ አመስግነው ወደቤታቸው ይገቡ የነበረበት ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በአካባቢያቸው የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሙስሊምና ክርስቲያን ሽማግሌዎች አብረው ለሽምግልና ይቀመጡ ነበር። የሃይማኖቶች ተቻችሎ፣ ተከባብሮ፡፣ ተማምኖ አብሮ የመኖ ነባር እሴታችን ይህ ነው።

እንግዲህ ጉባኤው በአቋም መግለጫው ይህ አገራዊ እሴት በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችል ትልቅ ዋጋ ያለው በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ነው የወሰነው።

ይህ ድንቅ እሴት ወደመጪው ትውልድ የመተላለፉን ጉዳይ እንደከዚህ ቀደሙ እንከን ሳይገጥመው መከናወኑ  ፈተና እየተጋረጠበት መሆኑ ሊስተዋል ይገባል። በዚሁ ርዕስ በቀረበው ክፍል አንድ ፅሁፍ በግቢያ ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአራቱ የሰፈነውን የአክራሪነት እንቅስቃሴ ለማሳየት ያነሳሁዋቸው ነጥቦች የመቻቻልና የመከባበር እሴታችን ከትውልድ ወደተውልድ የመተላለፉ ጉዳይ ሳንካ እየተጋረጠበት መሆኑን ያመለክታሉ።

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዜጎች የሚከተሉት ሃይማኖት የተለየ መሆን፣ በአንድ ሃይማኖትም ውስጥ የተለየ የተባለን አስተምህሮ በመከተላቸው፣ "እኛ ብቻ ነው ትክክል" በሚሉ አክራሪዎቸ ህይወታቸወን እንዲያጡ፣ አካላቸው እንዲጎድል፣ ንብረታቸው እነዲወድም … ተደርጓል። አክራሪዎች ባካሄዱት መጠነ ሰፊ የመናናቅና የጥላቻ ቅስቀሳ የመቻቻልና የመከባበር እሴት ውስጣቸው የሌላ በስሜት የሚነዱ ክፉ የአክራሪ ጀሌዎች ተፈጥረዋል።

ጉባኤው ያሳለፈው ሁለተኛው የአቋም መግለጫ ፣ "የህግ የበላይነት አስተሳሰብ በላቀ ደረጃ እንዲገነባ የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ህገመንግስትን የማወቅ፝ የማክበርና የማስከበር የዜግነት ድርሻቸውን ለመወጣት ጉባኤተኞቹ ቃል ገብተዋል" የሚለው ነው።

በዜጎች መሃከል፣ ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር ጉዳይ በዘመናችን ባለ የማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሥነ ምግባር ደንቦች ደረጃ  የሚተው ሳይሆን በህግም ጥበቃ ይደረግለታል። በሕገመንግስታችንና ከሕገመንግስቱ በመነጩ ሌሎች ሕጎች ላይ ይህን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የሰፈሩት ለዚህ ነው፡ ዜጎች ይህን ተከባብሮና ተቻችሎ በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችለንን የህገመንገስትና ሌሎች ከህገመንገስት የመነጩ ህጎች ድንጋጌዎች መረዳት፣ ሁሉም ዜጎች በእነዚህ ህጎቸ ፊት እኩል የመሆናቸውን የህግ የበላይነት መርህ መገንዘብ ከመገንዘብም አልፎ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ይህ ሲሆን ተከባብሮና ተቻችሎ መኖርን የማይቀበሉ "እኛ በህግም፣ ከሌሎች አመለካከቶችም የበላይ ነን" የሚሉ አጉራዘለል አክራሪዎችና ፅንፈኞች መላወሻ ቦታ ያጣሉ። ጉባኤተኞቹ አክራሪነትን በመከላከል ሰላም እንዲሰፍን በዚህ የአቋም መግለጫቸው ህገመንግስትን የማወቅ የማክበርና የማዝከበር የዜግነት ድርሻቸውን ለመወጣት ቃል የገቡት ለዚህ ነው።

ሶስተኛው የጉባኤተኞቹ የአቋም መግለጫ "በሃይማኖት ሽፋን እያቆጠቆጠ የመጣውን የአክራሪነትና ጽንፈኝነት እንቅስቃ፣ ምንም አይነት ሃይማኖታዊ መነሻ የሌለውና የጥቂት ቡድኖችን ድብቅ ፖለቲካዊ ፍላጎት ለማሳካት ያለመ በመሆኑ ጉባኤው በጋራ ለማውገዝና ለመመከት የጋራ አቋም ይዟል፡፡" ይላል፡፡

"የእኔ ሃይማኖት፣ የሃይማኖት አስተምህሮ የበላይ ነው፤ ወይም የበላይ መሆን አለበት" የሚል አመለካከት መለኮታዊ ወይም መንፈሳዊ መሰረት የለውም፡፡ የሃይማኖት ወይም የሃይማኖታዊ አስተምህሮ የበላይነት አጀንዳ መለኮታዊ ሳይሆን ምድራዊ ነው፡፡ ዓላማው በምድር ላይ የአመለካከት የበላይነትን ማግኘት ነው፡፡ ይህ የራስን አመለካከት የበላይ የማድረግ ፍላጎትና አቋም በምኞት ብቻ እንደማይሳካ ግልፅ ነው፡፡ ኃይልን መጠቀም ይሻል፡፡ ኃይልን መጠቀም ደግሞ የፖለቲካ የበላይነትን ወይም ስልጣንን የግድ ይላል፡፡

ይህ ዕውነታ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት እንቅስቃሴ በጉባኤው የአቋም መግለጫው ላይ እንደተመለከተው ሃይማኖታዊ መነሻ የሌለው፣ የፖለቲካ ፍላጎትን ማስጠበቅን ያለመ ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ በአመለካከት፣ በሃይማኖት . . . ሳይለያዩ አንዱ ለሌላው ባላጋራ ሳይሆኑ፣ በእኩልነት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችል ስርአት ለማስፈን አክራሪነትን የሚፀየፍ ትውልድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ የአክራሪነትና የፅንፈኝነት አመለካከትን ማውገዝ፤ ወደ ሕዝብ ውስጥ እንዳይገባ መመከት የግድ ነው፡፡

ጉባኤው ያወጣው አራተኛው የአቋም መግለጫ ከአክራሪዎች ጎራ ለተሰለፉ ከዚህ ሰልፍ እንዲወጡ ጥሪ የተላለፈበት ነው፡፡ የአቋም መግለጫው "በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለአገር ሰላም ጠንቅ ለሆነ የአክራሪ ኃይሎች የጥፋት መሳርያ የሆኑ አንዳንድ ወገኖች አደጋውን በውል ተገንዝበው ከስህተታቸው ታርመው ለሰላምና ለልማት በፅናት እንዲቆሙ ጥሪ ያቀርባል፡" ይላል።

ለሃይማኖት ወይም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ላይ ለተለጠፈ አመለካካት የበላይነት የሚደረግ የአክራሪነትና የፅንፈኝነት እንቅስቃሴ ሰላማዊ መንገድ አይመቸውም፡፡ ሁሌም የኃይልና የሁከት መንገድን ነው የሚመርጠው፡፡ በዚህ የኃይልና የሁከት መንገድ በሌሎች ላይ

የበላይነቱን ለማረጋገጥ በምክንያትና በዕውቀት ሳይሆን በስሜት የሚነዱ እንዲሁም ምንደኛ ጀሌዎች ያስፈልጉታል። ምንደኞቹና የሚሰሩትን የማያውቁ መናጆ ጀሌዎች የአክራሪው ቡድን መሳሪያ እንዳይሆኑ መነጠል የአክራሪነትን እንቅስቃሴ የማሽመድመድ የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡

በአገራችን ያለውን የአክራሪነት እንቅስቃሴ ስንመለከት እጅግ አብላጫ ቁጥር ያላቸው የአክራሪ ቡድን ጀሌዎች፤ የአክራሪነት እንቅስቃሴው የተንጠለጠለበት ሃይማኖት፣ ሕገመንግስቱና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ነው፡፡ በአብዛኛው እነዚህ ጀሌዎእ ክፉ ደጉን ያላገናዘቡ ስሜታዊ አፍላ ወጣቶች ናቸው።

እነዚህ በስሜት የሚነዱ ለጋ ወጣቶች በማያውቁት ጉዳይ ውስጥ ገብተው ስውር የፖለቲካ አጀንዳ ላላቸው ቡድኖችና ለፔትሮ ዶላር ቅጥረኞቻቸው ዓላማ ማሳኪያና ፍላጎት ማስፈፀሚያነት እየዋሉ ነው፡፡ እነዚህ በስሜት የሚነዱ የሌሎች ዓላማና ፍላጎት አስፈፃሚዎች ከአክራሪው ቡድን ከተነጠሉ አክራሪው ቡድን መንቀሳቀስ የማይችል በድን ነው የሚሆነው፡፡

እናም በተለይ ባለማወቅ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገውን አክራሪውን ቡድን እያገለገሉ የሚገኙ ወጣቶች ያሉበትን ሁኔታ ቆም ብለው እንዲያጤኑ መኮርኮር አስፈላጊ ነው፡፡ ትክክለኛውን እውነታ የተገነዘቡ ቀን የልማትና የሰላም መሳሪያ ወደ መሆን ይቀየራሉና፡፡

እንግዲህ ባለፉ ሁለት አስርት አመታት በሃገራችን ኢትዮጵያ የሃይማኖት ነጻነት መከበር በከፈተው ዕድል ተጠቅመው የአክራሪነት አመለካካትን ወደአገር ቤት በማስረግ በተለያዩ አካባቢዎች ነባሩን  የመቻቻልና የመከባበር እሴቶች የጣሱ በርካታ ፀያፍ ድርጊቶች ሲፈፀሙ ቆይተዋል፡፡ በተለይ ከአንድ ዓመት በፊት የአክራሪነት እንቅስቃሴ መሪዎቹ የመንግስትን ትዕግስትና የህዝቡን ዝምታ እንደፍርሃትና እንደአለማወቅ ቆጥረው የልብልብ ተሰምቷቸው ፀያፉን የአክራሪነት አቃማቸውን አደባባይ ላይ አውጥተውታል፡፡

በአገር ውስጥና በውጭ ተደራጅተው በሽብርተኝነት ከተፈረጁ ቡድኖች ጋር እንዲሁም የከሰረ አቋማቸው ከሕዝብ ካራቃቸው፣ እንዲሁም ሕጋዊና ሕገወጥ አካሄደን እንደአመቺነቱ

እያጣቀሱ ከሚንቀሳቀሱ ሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተቀናጅተው የአገሪቱን ሰላምና ተቻችሎ አብሮ የመኖር ዕሴት ለማፍረስ ሲፍጨረጨሩ ቆይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ የአክራሪዎቹ አካሄድ ከግዜ ወደ ግዜ ፀያፍነቱ እየተጋለጠ ድጋፍ እየራቀው፣ ከሃይማኖታዊነቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ገፅታው ፈጦ እየወጣ ትክክለኛ ማንነቱን ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያያን በሙሉ እየተገነዘቡት መጥተዋል። በዚህም ሳቢያ ራሱ አክራሪው ቡድን እና አክራሪውን ቡድን ተደግፈው የከሰረ ፖለቲካቸውን ለመሸጥ የቋመጡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕዝብ አየተተፉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት የሰላም ጉባኤ ደግሞ አክራሪውን ቡድን ከተለጠፈበት ሃይማኖት ላይ በመንቀል እርቃኑን ለማቆም፣ ከጀሌዎቹ በመነጠል ሽባ ለማድረግ፣ ሕገወጥ እንቅስቃሴ ሲያካሂድ በቀላሉ ሕጋዊና ተገቢ እርምጃ በመውሰድ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ሕልውናው እንዲያከትም ለመድፈቅ የሚያስችል ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ጉባኤው በአቋም መግለጫው ላሳለፋቸው ውሳኔዎች ሁሉም ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ ትኩረት ሰጥቶ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡